ቁ/ጉ 10,024
11/8/06

6.5-01/800
17 መጋቢት 2006

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Revenues and Customs Authority

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
በያሉበት፤

የንግድ ሚኒስቴር የክብደት መደብን መሰረት ያደረገ የግመል ድህረ-የመሸጫ ዋጋ በተመለከተ በቁጥር 01-85/20147 የካቲት 27 ቀን 2006 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ያስተላለፈውን መመሪያ ለተገቢው አፈፃፀም በዚሁ ደብዳቤ ሸኝነት የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጌጃበበ አስቻለው
የጉምሩክ/ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል
ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር

አባሪ፡- 19 ገጽ

ግልባጭ፤
- ለቅ/ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለኢ/ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድ ሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade


ቀን 27 የካቲት 2006
Date

ቁጥር 01-85/20147
Ref.No

ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- **<u>የግመል ድህረ የመሸጫ ዋጋ ቁጥጥር መመሪያን ይመለከታል።</u>**

ካሉ ችግሮች ውስጥ ከመሸጫ ዋጋ በታች ማስመዝገብ (underinvoicing) አንዱ ነው። ችግሩ ከሐገራችን ወደ ውጭ በሚላከው የምርት መጠን ልክ የውጭ ምንዛሪ እንዳናገኝ እያደረጉ በአንዳንድ የቁም እንስሳት ላኪዎች ላይም የሚታይ ሲሆን በተለይ ወደ ውጭ የሚላኩ ግመሎች የተለያየ የክብደት መጠን ያላቸው በመሆኑ እና በወቅቱ ያለው የብሔራዊ ባንክ የድህረ የመሸጫ ዋጋ ቁጥጥር የክብደት መጠንን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ከዋጋ በታች ማስመዝገብ (underinvoicing) ችግር በሰፊው ይስተዋላል።

በመሆኑም ችግሩን ለመፍታት የክብደት መደብን መሰረት ያደረገ የግመል ድህረ የመሸጫ ዋጋ ቁጥጥር መመሪያ በማዘጋጀት በመመሪያው ዙሪያ ሶስት የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት፣ ከቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማህበር፣ ከዋና ዋና የግመል ላኪዎች ጋር በመወያየት እንዲዳብር ተደርጓል።

በዚሁ መሰረት ከመጋቢት 01ቀን 2006 ጀምሮ በመመሪያው መሰረት ወደ ተግባር መግባት እንዲቻል መመሪያውን እና መመሪያውን ለማዳበር የተደረጉ የውይይት ቃለ ጉባኤዎችን አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>
ለቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማህበር


251-11-551 80 25-29
Fax 251-11-551 54 11
553 10 27, 552 24 19
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa Ethiopia

# ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎች የመሸጫ ዋጋ ድኅረ-ክትትል

# መመሪያ ቁጥር 004 / 2006ዓ/ም

ንግድ ሚኒስቴር ፣

መጋቢት 2006 ዓ.ም.

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
Ethiopian Revenues and Customs Authority

# ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎች የመሸጫ ዋጋ ድኅረ-ክትትል መመሪያ ቁጥር

## 004/2006 ዓ/ም

### መግቢያ

የቁም እንስሳትን ግብይት ለማሳለጥ እንዲቻል ለሀገር ውስጥም ሆነ ለወጭ ገበያ በሚቀርቡ የቁም እንስሳት የግብይት ሂደቱ ላይ የሚያጋጥሙ ዝርዝር ችግሮችን በመለየት ከእያንዳንዱ ችግር አንጻር መፍትሔ ሰጪ እና ሕጋዊ መሠረት ያለው ዝርዝር የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከዚህ አንጻር እያጋጠሙ ካሉ ችግሮች መሐል አንዱ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎች አንዳንድ ላኪዎች የሸጡበትን ዋጋ አሳንሰው ለብሔራዊ ባንክ በማስመዝገብ ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ትክክለኛ· የውጭ ምንዛሪ እንዳታገኝ የማድረግ ሕገ-ወጥ ተግባር እየተስተዋለ በመሆኑ፣

ብሔራዊ ባንክ እስካሁን ላኪዎች ግመሎችን ወደ ውጭ ሲልኩ ያስመዘገቡትን ዋጋ ከወቅቱ (ከወሩ) አማካይ መሸጫ ዋጋ ጋር በማነጻጸር ላኪዎች ከዋጋ በታች መሸጥ አለመሸጣቸውን የሚያረጋግጥበት የክትትልና የቁጥጥር የአሠራር ሥርዓት በአነስተኛ ዋጋ ሸጫለሁ በማለት ለብሔራዊ ባንክ በሐሰት እያስመዘገቡ ያሉትን አንዳንድ ላኪዎችን መቆጣጠር ባለማስቻሉ! በተቃራኒው ደግሞ አነስተኛ ክብደት ያላቸው ግመሎችን ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ሐቀኛ ላኪዎችን እርግጠኝነት በጎደለው መረጃ መነሻነት ከዋጋ በታች አስመዝግባችኋል በሚል መጉላላት እያስከተለባቸው በመሆኑ በአጠቃላይ ይህ የአሠራር ሥርዓት ውጤታማ ሆኖ ባለመገኘቱ፣

የዚህ የቀድሞ የአሠራር ሥርዓት ክፍተት ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎች የክብደት መጠን ልዩነትን መሠረት ያለማድረጉ ሲሆን ይህን መሰሉ አሰራር ለግመል፣ ለበግ እና ለፍየል ግብይት ተግባራዊ ባለመደረጉ አሁን ይህን የክብደት መጠንን ልዩነት መሠረት ያደረገ የመሸጫ ዋጋን የተከተለ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ግብይቱን በመከታተልና በመቆጣጠር ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት እንደሆነ በመታመኑ፣

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር-691/2003ዓ/ም አንቀጽ- 21 ንዑስ አንቀጽ-1/ሐ/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### 1- <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመርያ ‹‹ *ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎች የመሸጫ ዋጋ ድኅረ-ክትትል መመሪያ ቁጥር 004/2006ዓ/ም* ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2- <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ !

1. ‹‹ አዋጅ ››ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር-691/2003ዓ/ም አንቀጽ- 21 ንዑስ አንቀጽ-1/ሐ/ ማለት ነው።

2. ‹‹ ዋጋ አሳንሶ መሸጥ ›› ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎችን የክብደት መደብ ክፍፍል መሠረት አድርጎ በወሩ ካለው አማካይ የመሸጫ ዋጋ ከ15% በታች ዝቅ ባለ ዋጋ መሸጥ ወይም ሸጫለሁ ብሎ ለብሔራዊ ባንክ ማስመዝገብ ነው፣

3. ‹‹ ባንኮች ›› ማለት የባንክ ሥራ እንዲሰሩ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጣቸው ኩባንያዎች ወይም የመንግሥት ባንኮች ናቸው፣

Archives
መዝገብ ቤት

4. ‹‹ የክብደት መደብ ›› ማለት ግመሎችን የክብደት መጠናቸውን መነሻነት አነስተኛ ( small)ወይም መካከለኛ young/ ወይም ትልቅ adult/ ወይም በጣም ትልቅ mature/ ብሎ መለየት ነው፣

5. ‹‹የባንክ ሠነድ ›› ማለት ፕሮፎርማ ኢንቮይስ ወይም/እና ኮንትራት አግሪመንት ወይም/እና ሌተር ኦፍ ክሬዲት ወይም/እና የባንክ ፈቃድ ወይም/እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎች ግብይት አስፈላጊ የሆነ ሌላ ማንኛውም በባንክ አሰራር ሂደት ውስጥ ያለ ሠነድ ነው፣

6. ‹‹ ባለድርሻ አካላት ›› ማለት ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ ግመሎች ግብይት ሂደት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ የግብርና ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ ባንክ፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና የንግድ ሚኒስቴር ናቸው፣

## ክፍል ሁለት

## የድኅረ-ክትትል ተግባራት

3. የክብደት መደብ ክፍፍል (weight category)

1/ ግመሎችን የሚከተለውን የክብደት መጠን መሠረት በማድረግ !

ሀ/ ከ250 ኪሎ ግራም እስከ 320 ኪሎ ግራም የሚመዝን አነስተኛ( small) ግመል፣

ለ/ ከ321 ኪሎ ግራም እስከ 420 ኪሎ ግራም የሚመዝን መካከለኛ/ young ግመል፣

ሐ/ ከ421 ኪሎ ግራም እስከ 600 ኪሎ ግራም የሚመዝን ትልቅ /adult/ ግመል፣

መ/ 601 ኪሎ ግራም እና ከ601 ኪሎ ግራም በላይ የሚመዝን በጣም ትልቅ

(mature) ግመል፣ በሚል የክብደት መደብ ተከፋፍለዋል።

4. <u>ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎች የመሸጫ ዋጋ የድኅረ-ክትትል ስርዓት</u>

1/ በአንቀጽ 6 መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎች የወሩ የሚያወጣው አማካይ የመሸጫ ዋጋ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ግብይት በአንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት የክብደት መደብ ክፍፍልን የተከተለ መሆን አለበት፣

5. <u>የላኪ ግዴታ</u>

1. ግመሎችን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ላኪ የሚያቀርባቸው እያንዳንዱ የባንክ ሠነዶች ማለትም ፕርፎርማ ኢንቮይስ ፣ ኮንትራት አግሪመንት፣ ሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ የባንክ ፈቃድ እና ለግብይቱ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የባንክ ሠነዶች በአንቀጽ 3 መሠረት የእያንዳንዱን ግመል የክብደት መጠንና የክብደት መደብ የሚያመለክት መሆን አለበት።
2. የግመሎችን ክብደት በተመለከተ ግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብነት ያለው አካል የሚሰጠውን ውሳኔ የመቀበል፤
3. የየእለቱን የግመል ግዢና የኤክስፖርት ሽያጭ ብዛት እና ዋጋ መዝግቦ የመያዝና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ይህንኑ መረጃ የመስጠት፣
4. የሐገሪቱን ጥቅምና መልካም የንግድ ገጽታ ከሚያጎድፉ ተግባራት የመቆጠብ፤

6. <u>የብሔራዊ ባንክ ተግባራት</u>

1) የንግድ ባንኮች በላኪዎች የሚቀርቡ ሰነዶች በአንቀጽ 3 የተገለጸውን የክብደት ክፍፍል መሰረት ባደረገ መልኩ ያቀረቡ ላኪዎችን ብቻ እንዲያስተናግዱ ለሁሉም ንግድ ባንኮች መመርያ ማስተላለፍ፣
2) ወቅታዊ መረጃን መሠረት በማድረግ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎችን በአንቀጽ 3 የተገለጸው የክብደት መደብ ክፍፍል መሠረት አድርጎ የየወሩን አማካይ የመሸጫ ዋጋን ያወጣል፣

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade Archives
መዝገብ ቤት

3) በወሩ ግመሎችን ለውጭ ገበያ ዋጋ አሳንሶ የሸጠን ወይም ሸጫለሁ ብሎ ያስመዘገበን ላኪ ይለያል፣

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የለያቸው ላኪዎች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል

5) የወሰዳቸውንም እርምጃወች ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያሳውቃል

6) ሚኒስቴሩ በሚጠራው የባለድርሻ አካላት የምክክር ስብሰባ ላይ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት ይዞ ይገኛል።

7. የግብርና ሚኒስቴር ተግባራት

1/ ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ ግመሎችን ጤና በመመርመር የጤና መስፈርት ሳሟሉት ግመሎች የእንሰሳት ጤና ሰርተፍኬት ለላኪው ይሰጣል፣

2/ የእንሰሳት ጤና ሰርተፍኬቱን ከመስጠቱ በፊት ላኪው ያቀረባቸው የባንክ ሰነዶች በአንቀጽ 5 መሠረት የእያንዳንዱን ግመል የክብደት መጠንና የክብደት መደብ የሚያመለክቱ እና በተጨባጭ የሚላኩትን ግመሎች የሚገልጹ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት ፣ይህን የማያረጋግጡ ከሆነ ሰርተ ፍኬቱን መስጠት የለበትም፣

3/ ሚኒስቴሩ በሚጠራው የባለድርሻ አካላት የምክክር ስብሰባ ላይ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት ይዞ ይገኛል።

8. የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባራት

1) የቀረቡትን መረጃዎች ከእንሰሳቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማመሳከር ህጋዊነቱን ማረጋገጥ እና ህግ ተላልፈው ሲገኙ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ።

2) ወደ ውጭ የተላኩ ግምሎችን መጠን፣ ቀን፣ ላኪ፣ ተቀባይ/ ገዢ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃወችን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይልካል።

3) ሚኒስቴሩ በሚጠራው የባለድርሻ አካላት የምክክር ስብሰባ ላይ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት ይዞ ይገኛል።

ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቡድን Ethiopian Revenues and Customs Authority

9. <u>የንግድ ሚኒስቴር ተግባራት</u>

1/ በወሩ ግመሎችን ለውጭ ገበያ ዋጋ አሳንሶ የሸጠ ወይም ሽጫለሁ ብሎ ያስመዘገበ ተብለው የተለዩ እና በብሔራዊ ባንክ እርምጃ በተወሰደባቸው ላኪዎች ላይ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣

2/ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ወደ ውጭ የተላኩ ግመሎችን መጠን፤ቀን፤ላኪ ተቀባይ/ ገገር እና ሌሎች ተያያዥ መረጃወችን ይወስዳል ፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የብሔራዊ ባንክን የድኅረ መሸጫ ዋጋ ቁጥጥርን በሚያግዝ መልኩ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ ግመሎች ግብይት ሂደት አሳሳች ድርጊት በፈጸመ ወይም/እና ዋጋ አሳንሶ በሸጠ ወይም ሸጫለሁ ብሎ ባስመዘገበ ወይም/እና ይህን መመሪያ በመተላለፍ ሌላ ጥፋት በፈጸመ ላኪ ወይም ማንኛውም ሰው ላይ የወንጀል ወይም/ እና የፍትሐ ብሔር ክስ ይመሰርታል፣ አስተዳደራዊ እርምጃም ይወስዳል፣

4/ የዚህን መመርያ አፈጻጸም እና የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት አስፈላጊውን ማስተካከያ ይወስዳል፣

4/ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት የባለድርሻ አካላት የምክክር የስብሰባ መድረክ ያዘጋጃል፣ ለስብሰባው አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዩችን ያመቻቻል።

10. <u>የባለድርሻ አካላት የምክክር ስብሰባ ዓላማ</u>

ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ ግመሎች የግብይት ሂደት ላይ ባለድርሻ አካላት በሚገጥሟቸው ችግሮች እና የአሰራር ክፍተቶች ላይ በጋራ በመወያየት ለችግሮች መፍትሔ በመስጠት እና የተሻለ የአሰራር ስልት በመቀየስ ግብይቱን ዘመናዊ ማድረግና በዚሁ ግብይት ለሀገሪቱ ተገቢውን የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ነው።

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade Archives

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documents

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11. ቅጣት

1. ማንኛውም ግለሰብ ይህን መመርያ ተላልፎ ሲገኝ ብሔራዊ ባንክ ከመሸጫ ዋጋ በታች ማስመዝገቡን (under invoicing) በተመለከተ ባስቀመጠው ህግ መሰረት የሚቀጣ ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ1 የተገለጸው የወንጀል ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ በንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2006 አንቀጽ 61 እና በሌሎች ህጎች በተሰጠው ስልጣን መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

12. የተሻሩ አሰራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጋጩ ሌሎች መመሪያዎች ወይም የተለምዶ አሰራሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

13. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ የማሻሻል ወይም የመሻር ሥልጣን የሚኒስቴሩ ነው፡፡

14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ መጋቢት01 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ከበደ ጫኔ

የኢፌዲሪ ንግድ ሚኒስቴር ሚኒስትር

# የግመል የመሸጫ ዋጋ ድህረ ክትትል ላይ ያለውን የአሰራር ክፍተት ለመሙላት የተዘጋጀ ረቂቅ መመርያ ላይ የተደረገ ውይይት ቃለ ጉባዔ

የስብሰባ ቦታ ------------------- የንግድ ሚኒስቴር ስምንተኛ ፎቅ የስብሰባ አዳራሽ

ቀን 11/04/2006 ዓ.ም

ሠዓት 8:30

የስብሰባው ተሳታፊዎች

| | |
|---|---|
| 1) አቶ ኑረዲን ሞሃምድ | ሰብሳቢ |
| 2) ከሊፋ ሁሴን | ሰብሳቢ |
| 3) ዶ/ር ኪሚያ መሃመድ | በግብርና ሚኒስቴር ተወካይ |
| 4) ሀብቴ ትግሮ | የብሔራዊ ባንክ ተወካይ |
| 5) ፊቃዱ ጌታቸው | የቁም እንስሳት ግብይት ቡደን መሪ<br>ጽሁፍ አቅራቢ |
| 6) ሳሙኤል ብርሀኔ | የቁም እንስሳት ግብይት ቡድንረዳት ባለሞያ |

## የስብሰባው አጀንዳ

የግመል የመሸጫ ዋጋ ድህረ ዋጋ ቁጥጥር ላይ የሚታየውን የአሰራር ክፍተት ለመሙላት የቀረበ የመፍትሄ ሀሳብ ላይ ውይይት ማድረግ

ለውይይት መነሻ የግመል የመሸጫ ዋጋ ድህረ ዋጋ ቁጥጥር ላይ የሚታየውን የአሰራር ክፍተት ለመሙላት የታሰበ ሁለት አማራጮች የቀረቡ ሲሆን፣

አማራጭ አንድ

በዚህ የመፍትሄ ሀሳብ ግመሎች በክብደት መጠናቸው በመከፋፈል ከክብደቱ አንጻር ሊኖረው የሚገባውን ዋጋ ከግምት በማስገባት በዚሁ አግባብ ቁጥጥር ማድረግ ነው።

አማራጭ ሁለት

በዚህ የመፍትሄ ሀሳብ ለዳልጋ ከብት እንደተቀመጠ ሁሉ ለግመል ዝቅተኛ የኤክስፖርት ክብደት ማስቀመጥ ነው

በሁለቱም አማራጭ ሀሳቦች ላይ ውይይት ተደርጓል በዚሁ መሰረት ሃሰቦቹ በተለያየ መንግድ ተንሸራሽረዋል።

**ዶ/ር ኪሚያ ከግብርና ሚኒስቴር**

የሚሸጡበት ገበያ ስለሚለያይ ወይም መዳረሻ ገበያቸው የተለያየ ስለሆነ በአንድ ላይ የሁሉንም አማካይ ወስዶ መስራቱ አይከብድም ወይ?

ለባንክ በሚያስመዘግቡበት ወቅት ላኪዎቹ በግምት ነው የሚሞሉት የእንስሳቱን ክብደት በሚሞሉበት ወቅት ትክክለኛነቱ ምን ያህል አሰተማማኝ ነው? ሊጠየቁ የሚችሉትስ በምን አግባብ ነው? መነሻ እና መድረሻ ገበያው ተለይቶ ቢሰራ ምክንያቱም የሚሸጡበት ገበያ የተለያየ ስለሚሆን። ክብደት እና ዝርያን በተመለከተ የተለያየ ዝርያ ያላቸው የተለያየ ክብደት ነው የሚኖራቸው የሚል ሀሳብ አንስተዋል ከዚህ በተጨማሪ በረቂቅ መመሪያው ዙሪያ ላኪዎችም ቢወያዩበት የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።

ከብሔራዊ ባንክ አቶ ሀብቴ ትግሮ

የመደብ ክፍሉ ሬንጁ በዝቷል ስለዚህ በመሃል ያለውን ጋፕ ብንቀንሰው ከዋጋ በታች ያስመዘገቡ ሰዎችን የምንለይበት የነበረውን 15% ወደ 10% ዝቅ ቢል? ቅድመ እና ድህረ ቁጥጥር ብናደርግ?

በአቶ ከሊፋ በኩል ለተነሱት ሃሳቦች የተሰጡ ምላሾች

በመጀመርያ ደረጃ ኤክስፖረተሮች አብዛኞቹ ስምምነታቸው FOB ነው ይህም ማለት እስከ ወደብ ድረስ ብቻ ነው ሌላው በሁለተኛ ደረጃ የተለያየ ሀገር ስለተሸጠ ያን ያህል የጎላ ልዩነት የለውም ምክንያቱም አንዱ አገር በተሸለ ዋጋ እየገዛ ለሌላኛው አገር ዋጋ በጣም ወርዶ ሊሸጥ የሚችልበት ብዙም አሳማኝ ምክንያት አይኖርም ቢኖርም በ15% ውስጥ የሚካተት መሆን አለበት፡፡ ክብደት እና ዝርያን በተመለከተ መመርያው ሁሉንም የሚያስተናግድ ነው የሚሆነው ምክንያቱም ሁሉም እንደ ክብደቱ በተቀመጡት የክብደት መደብ ውስጥ የሚያርፍ ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም ዝርያ እንደ ክብደቱ የሚስተናገድ ነው የሚሆነው፡፡

ሌላው ከብሔራዊ ባንክ ለተነሳው ፡- መደብ ክፍሉ ሬንጁ በዝቷል ትንሽ ቢጠብ ለሚለው አነስተኛ 250-320 መካከለኛ 320-420 ትልቅ 420-600 በጣም ትልቅ 600 በላይ ቢሆን በሚል ሃሰብ ቀርቦ ስምምነት ላይ ተደርሷል ፡፡

ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ 15% የነበረውን ወደ 10% አስቸጋሪ ነው የሚሆነው የመመሪያውን ውጤት እያየን ብናስተካክለው የተሸለ ይሆናል አሁን ባለው ሁኔታ ቢቀጥል ነው የሚሻለው የሚል ሃሳብ በአቶ ከሊፋ ተነስቶእና በመመርያው ዙሪያ ዋናዋናየግመል ላኪዎች እንዲወያዩበት ቤቱ የተስማማበት ሆኖ የቀጣይ ስብሰባ ሰአትን በመወሰን ስብሰባው 11፡00 ሰአት ተጠናቋል ፡፡

የግመል የመሸጫ ዋጋ ድህረ ክትትል ላይ ያለው የአሰራር ክፍተት ለመሙላት የተዘጋጀ ረቂቅ መመርያ ላይ የተደረገ ውይይት ቃለ ጉባዔ

የስብሰባ ቦታ ------------------ የንግድ ሚኒስቴር ስምንተኛ ፎቅ የስብሰባ አዳራሽ

ቀን 24/04/2006 ዓ.ም

ሠዓት 8:30

የስብሰባው ተሳታፊዎች

| | |
|---|---|
| 1) አሰፋ ሙሉጌታ | ሰብሳቢ |
| 2) ከሊፋ ሁሴን | ሰብሳቢ |
| 3) ዶ/ር ኪሚያ መሃመድ | በግብርና ሚኒስቴር ተወካይ |
| 4) ሀብቴ ትግሮ | የብሔራዊ ባንክ ተወካይ |
| 5) ፍቃዱ ጌታቸው | የቁም እንስሳት ግብት ቡደን መሪ<br>ጽሁፍ አቅራቢ |
| 6) ሳሙኤል ብርሀኔ<br>ባለሞያ | የቁም እንስሳት ግብይት ቡድን ረዳት ባለሞያ |
| 7) ዮናስ አያሌው | ተሳታፊ |
| 8) ሰለሞን ገ/ህይወት | ተሳታፊ |
| 9) ሞገስ ሀይሌ | ተሳታፊ |
| 10)ሺበሺ ተሾመ | ተሳታፊ |
| 11)ክብሬ ሙላት | ተሳታፊ |
| 12)ዲና ገዛሀኝ | ተሳታፊ |
| 13)ምግስ አስፋ | ተሳታፊ |
| 14)ካሊድ አህመድ | ተሳታፊ |
| 15)ሰኢድ ንጉሴ | ተሳታፊ |
| 16)ተፈሪ ሀይሉ | ተሳታፊ |
| 17)ቴውድሮስ ተሸመ | ተሳታፊ |

የስብሰባው አጀንዳ

በግመል የመሸጫ ዋጋ ላይ የሚታየውን የአሰራር ክፍተት ለመሙላት ከላኪዎች ጋር የተደረገ ውይይት።

ከዚህ በፊት በተደረገው ውይይት በተወሰነው መሰረት ላኪዎች የተጠሩ ሲሆን ከዚህ በፊት በተደረገው ውይይት ላይ እንደተነሳው መመሪያው በሁለት መልኩ ቀርቧል ፣

አማራጭ አንድ

በዚህ የመፍትሄ ሀሳብ ግመሎች በክብደት መጠናቸው በመከፋፈል ከክብደቱ አንጻር ሊኖረው የሚገባውን ዋጋ ከግምት በማስገባት በዚሁ አግባብ ቁጥጥር ማድረግ ነው።

አማራጭ ሁለት

በዚህ የመፍትሄ ሀሳብ ለዳልጋ ከብት እንደተቀመጠ ሁሉ ለግመል ዝቅተኛ የኤክስፖርት ክብደት ማስቀመጥ ነው

በሁለቱም አማራጭ ሀሳቦች ላይ ውይይት ተደርጓል በዚሁ መሰረት ሃሳቦቹ በተለያየ መንግድ ለማንሸራሸር ተሞክሯል።

አቶ አሰፋ በመመሪያው አስፈላጊነት ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከሰጡ በኋላ በተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ላይ ተሳታፊዎች ሀሳብ ሰጥተዋል። የተሰጡ ሀሳቦች እና ጥያቄዎች

አቶ ሰለሞን

1) አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ይህን መመሪያ ይዞ ወደ ተግባር መግባት ይከብዳል የተወሰኑ ዝርዎችን ከገበያ ውጪ የሚያደርግ ይመስላል ለምሳሌ የአፋር ግመል እድሜውና ክብደቱ አይጣጣምም ከሌላው ዝርያ አነስ ይላል መመርያው ሊገድበው አይችልም ወይ?
2) የተሟላ የኳራንታይን ጣቢያ በሌለበት ሁኔታ መመርያው ለጉምሩክ እና ለኳራንታይን ጣቢያ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት በር አይከፍትም ወይ?
3) ኳራንታይን ሚዛን የለም ለሚለው መንግስት ይህን ማድረግ ያቅተዋል ብሎ ለማመን ይከብዳል ወይንስ ዘርፉን ዘንግቶታል ማለት ነው ምክንያቱም ስራው በቀላሉ በአንድ ግለሰብ ሊሰራ የሚችል ስራ ነው?
4) ለእያንዳንዱ ለተቀመጠው የክብደት መደብ ዋጋ ተወስኖ ቢነገረን?
5) በየጊዜው የሳምንት እና የወር ዋጋ እየተጠና ጠቋሚ መነሻ መረጃ በመህበሩ በኩል ቢደርሰን ?
6) ባለድርሻ አካላት በጉዳዩ ላይ ከእኛ ጋር ተገናኝተን ብንወያይበት ?
7) ገቢዎች እና ጉምሩክ እንኳን መመርያ አዋጁን እንደፈለጋቸው ነው የሚተረጉሙት ስልዚህ ይህን መመርያ ምን ያህል ይተረጉሙታል?

የተሰጡ ምላሾች

1) አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ይህን መመሪያ ይዞ ወደተግባር መግባት ይከብዳል የተወሰኑ ዝርዎችን ከገበያ ውጪ የሚያደርግ ይመስላል ለምሳሌ የአፋር ግመል እድሜውና ክብደቱ አይጣጣምም ከሌላው ዝርያ አነስ ይላል መመርያው ሊያግድበው አይችልም ወይ ለሚለው ጥያቄ መመርያው ሁሉንም እነደየክብደታቸው የሚያስተናግድ ነው የሚሆነው የተቀመጠው ክብደት መደብ ውስጥ እንደየክብደቱ በአንዱ ውስጥ ይካተታል ስሊዚህ የሚገደብ ዝርያ አይኖርም ::
2) የተሟላ የኳራንታይን ጣቢያ በሌለበት ሁኔታ መመርያው ለጉምሩክ እና ለኳራንታይን ጣቢያ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት በር አይከፍትም ወይ? ይህን እንደ መንግስት ሙስናን ለመዋጋት እያረገ ያለው ጥረት እንዳለ ሆኖ በመህል እኛም በኢንስፔክሽን ስራ ችግሩን ለመቆጣጠር የምንሄድበት ይሆናል እናንተም ከመስጠት መቆጠብ ይኖርባችኋል የሚል ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archive

3) ኳራንታይን ሚዛን የለም ለሚለው መንግስት ይህን ማድረግ ያቅተዋል ብሎ ለማመን ይከብዳል ወይንስ ዘርፉን ዘንግቶታል ማለት ነው ምክንያቱም ስራው በቀላሉ በአንድ ግለሰብ ሊሰራ የሚችል ስራ ነው ይህ ጥያቄ የእኛም ጥያቄ ነው ነገር ግን እኛም ዝም አላልንም ችግሩ መፍትሄ የሚያገኝበትን ሁኔታ ከማንኛውም ጊዜ በተሻለ እንሰራለን በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ ለማምጣትም እንጥራለን የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

4) ለእያንዳንዱ ለተቀመጠው የክብደት መደብ ዋጋ ተወስኖ ቢነገረን የሚል ጥያቄ ተነስቶ አሁን ያለው የግብይት ስርዓት የነጻ ገበያ መርህ ነው ስለዚህ በዚህ ስርዓት ቅድመ ግብይት ዋጋ ቁጥጥር ማድረግ አይቻልም ነገር ግን ይህ ሲባል ዋጋ ቁጥጥር አናደርግም ማለት አይደለም ድህር ግብይት ዋጋ ቁጥጥር የምናደርግብት አግባብ ይኖራል፡፡

5) በየጊዜው የሳምንት እና የወር ዋጋ እየተጠና በመህበሩ በኩል ጠቋሚ መነሻ ዋጋ ቢሰጠን ለሚለው ጥያቄ ጠቋሚ ዋጋ ሳይሆን አጠቃላይ ያለውን መረጃ የምናደርስ ይሆናል የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

6) ከመንግስት ባለድርሻ አካላት በጉዳዩ ላይ ከእኛ ጋር ተገናኝተን ብንወያይበት በሚል ለቀረበው ሀሳብ በቀጣዩ ሳምንት ጥር 02 2006 ከቀኑ ስምንት ሰዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመወያየት ቀጠሮ ተይዞ 11፤00 ስብሰባው ተጠናቋዋል፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

## የግመል የመሸጫ ዋጋ ድህረ ክትትል ላይ ያለው የአሰራር ክፍተት ለመሙላት የተዘጋጀ ረቂቅ መመርያ ላይ የተደረገ ውይይት ቃለ ጉባዔ

የስብሰባ ቦታ ------------------ የንግድ ሚኒስቴር ስምንተኛ ፎቅ የስብሰባ አዳራሽ

ቀን 02/05/2006 ዓ.ም

ሠዓት 8:30

የስብሰባው ተሳታፊዎች

| | |
|---|---|
| 1) ከሊፋ ሁሴን | ሰብሳቢ. |
| 2) ዶ/ር ኪሚያ መሃመድ | በግብርና ሚኒስቴር ተወካይ |
| 3) ሀብቴ ትግሮ | የብሔራዊ ባንክ ተወካይ |
| 4) ፍቃዱ ጌታቸው | የቁም እንስሳት ግብት ቡደን መሪ<br>ጽሁፍ አቅራቢ. |
| 5) ሳሙኤል ብርሀኔ | የቁም እንስሳት ግብይት ቡድን<br>ረዳት ባለሞያ ባለሞያ |
| 6) ሰለሞን ገ/ህይወት | ተሳታፊ |
| 7) ሺበሺ ተሾመ | ተሳታፊ |
| 8) ካሊድ አህመድ | ተሳታፊ |
| 9) በረከት ደመቀ | ተሳታፊ |
| 10)ጌታቸው በቀለተሳታፊ | ተሳታፊ |
| 11)ቴውድሮስ ተሸመ | ተሳታፊ |
| 12)ደስባለ ወ/ምህረተ | ተሳታፊ |

የስብሰባው አጀንዳ

የግመል የመሸጫ ዋጋ ድህረ ዋጋ ቁጥጥር ላይ የሚታየውን የአሰራር ክፍተት ለመሙላት የቀረበ የመፍትሄ ሀሳብ ላይ ውይይት ማድረግ፡፡ ከዚህ በፊት በአጀንዳው ዙሪያ በተደረጉ ሁለት ውይቶች ማብራሪያ ከተሰተ በኋላ የዚህን ውይት አስፈላጊነት በመጥቀስ እና የተደረሰበትን ውሳኔ በማስቀመጥ ውይቱ ተጀምሯል፣

የተነሱ ሀሳቦች

ወ/ሮ ክብሬ

1) የአንዳንድ ግመሎች ዝርያ የሚወፍረው በእድሜ ነው ስለዚህ ማወዳደሪያው በክብደት መሆኑ ቀርቶ በእድሜ ቢሆን
2) ብሔራዊ ባንክ ዋጋ ሲያወዳድር በአንድ ላይ ከሚሆን በመዳረሻ ገበያ ከፋፍሎ ቢሆን
3) መነሻ ዋጋ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል ቢቀመጥ

አቶ ሰለሞን

1) የዳልጋ ከብት መላክ ያለበት ከ320 ኪ.ግ በላይ መሆን እንዳለበት በመመርያ ተደንግጓል ነገር ግን እየተላከ ያለው ከ320 ኪ.ግ በታች ነው ፈጻሚው መመሪያውን አውቆ እንዲተገበር ለማደረግ ምን ዝግጅት ተደርጓል
2) የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት ተግባር እና ሀላፊነት በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል

ዶ/ር ኪሚያ

1) ኳራንታይን ጣቢያ ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች ምንም የተሟላ ፋሲሊቲ የለም ለስራ ቁጥጥር ስንወጣ ልንቆጣጠረው በምንወጣው ባለሀብት ተሸከርካሪ ነው የምንወጣው ለስራው የሚያስፈልጉ ግብአቶች ባልተሟሉበት ውጤት ማምጣት ይከብዳል ሊታሰብበት ይገባል ፡፡
2) ኤክስፖርተሮች ወደ ኳራንታይን ሲመጡ የውል ስምምነታቸውን ይዘው አይመጡም ይዘው እንዲመጡ ቢደረግ፡፡
3) እንስሳት ተጭነው መጥተው ባለቤታቸው ሲጠየቅ አይታወቅም ይህም አሰራሩ ላይ የራሱ ተጽዕኖ ስላለው ቢታሰብበት

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 3

4) የባለሞያ እጥረት ስላለ ቢሟላልን

በአቶ ከሊፋ በኩል የተሰጡ ምላሾች

1) በዋናነት የመመሪያው መውጣት ህጋዊ ኤክስፖርተሩን ለመደገፍ ነው በእኛ በኩል የተፈለገው ዋጋ መወሰን አደለም ትናንሽ ግመል የሸጡት ኤክስፖርተሮች ከዋጋ በታች ( under invoice) ተብለው እንዳይጠየቁ እና ትላልቅ ግመሎች ሸጠው ደግሞ በአነስተኛ ዋጋ የሚያስመዘግቡትን አሰራር ለመከላከል የተዘጋጀ ነው፡፡
2) ማወዳደርያው በክብደት መሆኑ ቀርቶ በእድሜ ቢሆን ለሚለው ጥያቄ በእድሜ ማወዳደሩ ትንሽ አስቸጋሪ ስለሚሆን ለመፈጸም የተሸለ የሚሆነውም ክብደትን መሰረት ባደረገ መለኩ መሆኑ የተሸለ ይሆናል፡፡
3) ብሔራዊ ባንክ ሲያወዳድር መዳረሻ ገበያን መሰረት ባደረገ መልኩ ለሚለው ያለው የዋጋ ልዩነት ብዙም የጎላ ስላልሆነ ቢኖርም በተያዘው 15% መጠባበቂያ ውስጥ የሚካተት ስለሚሆን በዚሁ መቀጠሉ የተሻለ ይሆናል መዳረሻ ገበያን መሰረት አድርጎ መስራቱ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡
4) ሀገራችን እየተከተለች ባለችው የነጻ ገበያ መርህ ነው ስለዚህ ቅድመ ዋጋ ቁጥጥር ማድረግ አይቻልም በመሆኑም መንግስት ቅድመ ዋጋ ቁጥጥር አያደርግም፡፡
5) በጉዳዩ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጎበታል ምናልባት በቀጣይ አፈጻጸሙ ላይ ክፍተት ሊኖር ይችላል ነገር ግን በመስክ ክትትል በማድረግ እና ከኤክስፖርተሮች መረጃ በማሰባሰብ ችግሩ ከስር ከስር የሚፈታ ይሆናል፡፡
6) የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ሀላፊነት በመመሪያው በግልጽ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡
7) የእንስሳቱ ባለቤት አይታወቅም ወደ ኳራንታን ሲመጡ የውል ስምምነታቸውን ይዘው አይመጡም ለሚሉት ጥያቄዎች ከማብራሪያ ጋር  አዋጁ በግልጽ የሚመልሳቸው ነው የሚሆኑት የሚል ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡ በዚሁ መሰረት በአጠቃላይ በተነሱት ሀሳቦች ላይ የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ እና በመመሪያው  አስፈላጊነት ላይ  የጋራ አቋም በመያዝ ውይይቱ11፤00 ሰዓት ተጠናቋል፡፡